# የፌደራል ሃይሎች የኣሰላለፍ ኣቅጣጫና ሚዛን

በዚህ ፅሁፍ የፌዴራል ሃይሎች ስንል፡ ኣሁን በስራ ላይ ያለው የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት መሰረት ኣድርገው የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች መብትና ስልጣን ለማስጠበቅ የሚታገሉ በህብረ ብሄራዊ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲ ኣምነው ለተግባራዊነቱ እየሰሩ ያሉ ሃይሎች ማለታችን ነው። እኒህ የፌደራል ሃይሎች በወቅቱ በኣነስተኛ፣ መካከለኛ እና ትልቅ በሚባል ድርጅታዊ መዋቅር፡ ቆመናና ብቃት፡ተደራጅተው ተመሳሳይ ስትራተጂ እና ዕላማ ይዘው በሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች በሰራ ላይ መኖራቸው ይታወቃል። ያለተመዘገቡና ሕጋዊ እውቅና ገና ያላገኙትን ለግዜው ኣቆይተን ቁጥራቸው ከ50 በላይ የፌዲራል ሃይሎች እናዳሉ ተጠንቷዋል።

ኣሁን ባለው ሁኔታ የህብረ ብሄራዊ ፌዲራል ሃይሎች ኣሰላለፍ እንደሚያመለክተው በሁለት ዋና ዋና ማእከሎች ቅንጅታቸውን ወደ ወሳኝ ምዕራፍ ለማሸጋገር በንቅናቄ ላይ እንዳሉ መረጃዎች ብግልፅ ያመለክታሉ። ማእከሎቹ **ኦሮምያና ትግራይ** ሲሆኑ በውሳኔ ወይ ምርጫ ማእከል እንዲሆኑ ተፈልጎ ሳይሆን ባለፈው 45 የትግል ፣ ስልጣንና ውጣ ውረዶች የንቅናቄ ኣመታት የፌዲራል ሃይሎች የፖለቲካ እና ወታደራዊ የሃይል ምንጭ ሆነው በማገልገል በፈጠሩት ተፅዕኖና ተሞክሮ ምክንያት ነው።

## 1. ኦሮምያ

ኦሮምያ ኣሁን ባለው የሃይሎች ኣሰላለፍ የፌዲራሊስት ሃይሎች የፖለቲካ ምህዋር ይቆጣጠራል። በዚህ ማእከል ወሳኝ ናቸው ተብለው የሚታወቁ ሰስት (3) ፌዲራሊስት የፖለቲካ ድርጅቶች ተሰማርቷል። የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (**ኦነግ**)፣ የኦሮሞ ፌዲራሊስት ኮንግረስ (**ኦፌኮ**) እና ብሄራዊ ፓርቲ ኦሮሞ (**ብፓኦ**) ሲሆኑ ፡ **ኦሮምያ** የሆነ መሰረታዊ ያልሆኑ ድክመት ካልተፈፀመ በስተቀር የፌዴራል የፖለቲካ ሃይሎች መርቶ ለድል ለማብቃት ታሪካዊ ሃላፊነት የተጣለበት ማእከል ሆነዋል። በዚ ምክንያት፡

**ሀ ፡** ሰስቱ በሕብረ ብሄራዊ ፈደራሊዝም ጎራ የተሰለፉ የኦሮሞ ሃይሎች 01/03/20፡ ጥምረት ፈጥረዋል። በጥምረታቸው የፖለቲካ ሳይንስ ምሁርና ውጤታማው ኣክቲቪስት ጀዋር መሃመድ ኦፌኮን በመቀላቀል በጥምረቱ ውስጥ ቄሮን ሳይከፋፈል ወደ ፌዲራሊስቶች እንዲያዞሮው ያስችለዋል የሚል ግምት ኣስይዞታል።

**ለ፡** ሰስቱም ድርጅቶች በመካከላቸው ሊደረግ የነበረው ፉክክር በማስወገድ የኦሮሞው ግዙፍ **180 የፓርላማ ድምፅ** ወሳኙን እና ኣብዛኛውን ሊያነሱ የሚያስችላቸው ኣሰላለፍ ኣድርጓል። በዚህ ኣሰላለፋቸው የኦሮምያ የመስተዳደር ክልልና ብሃገር ደረጃ ለማሸነፍ የሚያበቃቸው ከዚህ ኦሮምያ ክልል በማንሳት ኢህኣዴግን የተካው የብልፅግና ፓርቲን በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያሸንፉ የሚጠበቅ ኣድርጎታል።

**ሐ፡** ድርጅቶቹ በተለይ **ኦነግ** እና **ኦፌኮ** (መድረኽ) ከኦሮሞ ውጭ ባሉት ክልሎች **ከኣርባ** በላይ ኣነስተኛና ማእከላዊ ኣቅም ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች እና ቡድኖች በዘጠኙ ክልሎች በማእቀፋቸው በማሰባሰብ በደቡብ፣ሶማሊያ፣ኣፋር፣ ቢንሻንጉል ጉምዝ፣ እና ጋምቢላ ክልሎች ተመጣጣኝ ድምፅ በኣንዳንዶችም **123** የፌዲራል ድምፅ ያለው የደቡብ ክልል በተለይ በሲዳማ **የሲዳማ ነፃነት ንቅናቄ** እና የፕሮፌሰር በየነ ጵጥሮስ ድርጅቶች የሚወዳደሩበት ወሳኙን የማሸነፍያ ድምፅ ለማንሳት የሚያስችላቸው ኣቅጣጫ እንደሆነ ለማመን የሚከብድ ኣይመስልም። ከሁሉም በላይ ልዩ ትክረት እየሳበ ያለው **የቅማንት እና ቤንሻንጉል** ጉምዝ ብሄረሰብ ጀኖሳይድ ፣ብዩኒቪርስቲዎች፡ ግድያ፡ በቤተ እምነት ቃጠሎ እየተፈፀመበት ያለው የኣማራ ክልል ነው።

በዚህ ክልል ባጠቃላይ የፌዲራል ሃይሎች **136** የክልሉ የፌዲራል ፓርላማ ድምፅ ተጋርተው ወይ ኣሸንፈው ሊወጡ እንደሚችሉ ግምቱ እየሰፋ ሄዷል። በኦነግ ዙርያ እየተሰባሰቡ ያሉት **የቅማንት**ና **ኣገው** ዲሞክራሲያዊ ፓርቲዎች እንዲሁም **የወሎና ሸዋ** ኦሮሞ ዞኖች በዚህ ምርጫ በፌዲራሊስት ጎራ ተሰልፈው ተፅእኖ ፈጣሪ እንደሚሆኑ የሚያጠራጥር ኣይደለም። በቅርቡ ብምስራቅና ደቡብ ኦሮምያ (በሃረርና ኣሩሲ) ኣካባቢ በኦፌኮ መሪነት ከህዝብ ጋር ለማስተዋወቅ በተካሄዱት የቅስቀሳ ዘምቻ በመቶዎች ሺ የሚቆጠር ህዝብ ኣንቀሳቅሷል። ይህ ቅስቀሳ በወላዋዩ ብልፅግናና በኣሃዳውያን ካምብ መደናገጥ ከመፍጠሩ በላይ ስም የማጥፋትና ምርጫውን የተሳካና ዲሞክራስያዊ እንዳይሆን ከወዲሁ ለማድረግ ውጥኖች ማሳየት ጀምሯል።

## 2. ትግራይ፡

ይህ የፌደራሊስቶች ማእከል **ህወሓት** ባለፈው 27 የስልጣን ዘመኑ በዲሞክራሲና ሰብኣዊ መብት ጥሰት የነበርው ድክመት እንደተጠበቀ ሆኖ በህብረ ብሄራዊ ፌዴራሊዝም ያለው ኣቋም ግን በጥያቄ ውስጥ ሊገባ ኣይችልም። ኣሁን ባለው የሃይሎች ኣሰላለፍ ደግሞ **ህወሓት** ከ**ብልፅግና** እና **ኢዜማ** ጋር ባለው የተካረረ ተቃርኖ ምክንያት እና የትግራይ ህዝብ ላእላውነቱ ለማስጠበቅ ባለው ጠንካራ ኣንድነትና ኣቋም የህብረ ብሄራዊ ፌዲራል ሃይሎች ከማንም ግዜ በላይ በንቃት ተጠናክረውና ኣሸንፈው እንዲወጡ ጠንክሮ እየሰራ መሁኑን ነው የሚታወቀው። 01/16/2020 መቐለ ላይ በህወሓት ኣስተባባሪነት **34 የፌዴራል** ኣናሳ ድርጅቶች የጋራ ጥምረት ፈጥሯል። ህወሓትን ጨምሮ ትግራይ ውስጥ የሚገኙ 5 የፖለቲካ ተቀናቃኝ ድርጅቶች ማን ያሸንፍ ማን የክልሉ **38 የፌደራል ድምፅ** ሳይሸራረፍ ለህብረ ብሄራዊ ሃይሎች ተቆጥሮ በባንክ እንደ ተቀመጠ ንብረት ይቆጠራል።

ስለዚህ በትግራይ ለፌደራሊዝም የተወካዮች ድምፅ ለማግኘት የሚደረግ ፉክክር ኣሳሳቢ ኣይደለም። በኣረናና ህወሓት የሚደረግ ፉክክር ሁለቱም ህብረ ብሄራዊ ፌዴራሊዝም የሚከተሉ በመሆናቸው ባገር ደረጃ ለፌዴራሊስቶች የሚያሳስብ ኣይደለም፡ ህወሓት የብልፅግና ኣካል ቢሆን ኖሮ ነበር ኣሳሳቢ ሊሆን የሚችል የነበርው። ድርጅቶቹ ለቀጣዮቹ ምርጫዎቻቸው ለትግራይ ክልል መስተዳደር የህዝብ ተወካዮች ኣብላጫ ድምፅ ለማግኘት የሚያደርጉት ውድድር ጠንከር እና መርረ ይላል ብሎ መገመት ግን ይቻላል።

በዚህ ማእከል ተጨማሪ ተልኮ ኣለ ከተባለ **ከምርጫ በኃላ** ለሚፈጠር ለሚችል ችግር ነው። ምርጫው ሊጭበረበር ይችላል። ኣሸናፊ ማን ሊሆን እንደሚችል የፌደራል ሃይሎች ባላቸው ዝግጅት ከወዲሁ መገመት ይቻላል። ዶ/ር ኣብይና ፓርቲያቸው **ብልፅግና** ምርጫው ያጭበረብሩታል ብሎ

መደምደም ባይቻልም በአፍሪቃውያን ባጠቃላይ እና የባለፉት ዘመናት የኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ቆሻሻ እና ኣሳፋሪ ተግባራት መነሻ በማድረግ የማንጠረጥርበት ምንም ምክንያት የለም።

ይህ ምርጫ በሰላማዊ መንገድ ከተካሄደ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ በይዘቱና ብዲሞክራሲያዊነቱ የተለየና የመጀርያ ይሆናል። ምርጫው በትክክል ካልተካሄደ ግን እንደተለመደው ዘው ብሎ በስልጣን መቆየት የሚቻል ኣይሆንም። ሁኔታዎች ተቀያይረዋል። ትግራይ በስልጣን ላይ ያለች የፌዴራሊስቶች የሃይል ምንጭ ሆና የምትቀጥልበት ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል። የትግራይ ህዝብ እና በውስጡ ያሉ የተደራጁ ሃይሎች በበኩላቸው ለፌደራሊዝም ያላቸው ታማኝነት እና የትግራይ ህዝብ በግዛታዊ ኣንድነቱ ዙርያ ሊመጣው የሚችል ኣደጋ እየተከላከሉ የፌደራል ሃይሎች ኣሸንፈው እንዲወጡ ጠንክሮ እየሰራ ያለ ህዝብና ክልል ነው።

## የኣንድነት (ኣሃዳዊ) ሃይሎች

ኣሃዳዊ የሚባሉ ቢያንስ ኣሁን በስራ ላይ ያለው ህገ-መንግስትና ህብረ ብሄራዊነት ታሳቢ ኣድርጎ የተዋቀረው ፌዴራሊዝም ለማፍረስ የሚታገሉ ሃይሎች ማለታችን ነው። ኣሁን ባለው ሁኔታ ኣስር (10) የሚሆኑ የተለያዩ ኣናሳ ድርጅቶች በማሰባሰብ ብውህደት የተመረተ **ኢዜማ** የተባለ ፓርቲ እና እንደ የኣዲስ ኣበባው **ባልደራስ** የመሰሉ ሊያስከትል የሚችል ቁመና ይዘዋል። **ኢዜማ** ብግልፅ ቋንቋ ብፕሮግራም ደረጃ የኣሃዳዊ ፖለቲካ ስርኣት ኣራማጅ ተብሎ የተለየ ሃይል ነው። ይህ ሃይል በቀላሉ ባይታይም በህዝብ ድምፅ ከሚያገኘው ድል ብተንኮል፥ በቆዩ የዲፕሎማሲ ኣሻጥሮችና ስም በማጥፋት ዘመቻዎች በማራመድ የበለጠ ችሎታ እንዳልው ይታወቃል። ኢዜማ በህግ ጭምር የብሄር ድርጅቶች መከልከል ኣለባቸው ብሎ ያምናል። ኢትዮጵያ የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች የሚኖርባት ኣገር ስለሆነች በዋናነት የህብረ ብሄራዊ ፌዴራሊስት ሃይሎች ግዛት ነች። ይህ ከሆነ ኢዜማ በየትኛውም ክልል ከኣዲስ ኣበባ ውጭ ሊያሸንፍ እንደሚችል ኣይታወቅም።

በኣማራ ክልል በስፋት ቢወዳደርም የተወሰነ ድምፅ ከማግኘት ውጭ ውጤት ይኖሯል ተብሎ ኣይጠበቅም። ኣዲስ ኣበባን ጨምሮ በኦሮምያ እና ደቡብ ክልል በሚገኙ ድብልቅ ብሄራዊ ተዋፅኦ ያልዋቸው ከተሞች ጠንካራ ተፎካካሪና በተወሰነ ደረጃም ውጤት ያስመዘግባል ቢባልም በክልል ሆነ ባገር ኣቀፍ ደረጃ ለማሸነፍ የሚያበቃው ኣይሆንም። በኣማራ ክልል፡ ኣማራ ብሄራዊ ንቅናቄ (**ኣብን)** በሃገር ደረጃ ከማን ጋር ጥምረት እንደሚፈጥር ባይታወቅም በዚህ ክልል የማይናቅ ውጤት ይኖሯል።

## ብልፅግና እንደ ወላዋይ

ከህግ ማእቀፍ ሊነሱ የሚችሉ ለህግ ባለሞያዎች ትተን **ብልፅግና** ኢህኣዴግን ተክቶ ብስልጣን ላይ ያለ **ወላዋይ** ሃይል ነው። በኣሃዳውያን እና ፌዲራሊስት ሃይሎች መካከል የሚደረግ ታሪካዊ እና ወሳኝ ፍልምያ ብማጭበርበር ጭምር ኣደጋ ባገሪቱ እንዳይደግስ ይጠረጠራል። በቅርቡ ኢህኣዴግን በማፍረስ ራሱን ወደ ብልፅግና የሚል ስም የቀየረ ፓርቲ ነው። የፖለቲካ ፕሮግራሙ ህብረ ብሄራዊ ፌዴራሊዝምን የሚቀበል ይመስላል። በተግባር እያረጋገጠው የመጣ ኣሰላልፍ ግን ለኣሃዳውያን እንደሚቀርብ ነው። የድሮ **ኦህዴድ** በኦሮሞ ሊኖሮው ይችል የነበረ ተቀባይነት በብልፅግና ፓርቲ ተዋህዶ በመስመጡ ምክንያት የኦሮሞ ሙሁራንና የፖለቲካ ሊህቃን በወሰዱት የተቀናጀ ዘመቻ ጠ/ሚ/ር ኣብይ ኣህመድ እና ፓርቲያቸው ብልፅግና ከመቃብር በታች ድምፅ ኣልባ እንዲሆን

ኣድርገውታል። **ኣቦ ለማ መግርሳ** የቲም ለማ ፈጣሪ በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ትልቅ ተፅእኖ በመፍጠር የታወቁት ፖለቲከኛ ብልፅግናን ተቃውመው ሰልፋቸው ከኦሮሞ ፌዴራሊስት ሃይሎች ሆኗል።

በኣዲስ ኣበባ፣ ኣማራ ክልል፣ እና በኦሮምያ ትላልቅ ከተሞች እንዲሁም በተወሰኑ የገጠር ወረዳዎች በእጁ ያለ መንግስታዊ መዋቅር በመጠቀም ጭምር ተፎካካሪ እንደሚሆን ይጠበቃል። ተፎካካሪነቱ ግን በኦሮምያ፡ ትግራይ፡ ሶማሊያ፡ ኣፋር፡ እና ደቡብ ክልል ከመሸነፍ ሊያድነው ኣይችልም። በኣማራ ክልልም ተጋርቶ (ተካፍሎ) እንጂ ብሙሉ ኣሸንፎ የሚወጣበት ኣጋጣሚ የለም። እንደሚሸነፍ ምንም ኣያጠራጥርም። ድህረ ምርጫ ከ**ኢዜማ** ሊያሳካው የሚችል የጥምር መንግስት ታሳቢ ቢያደርግም በቂ ድምፅ ሊሆንለት ኣይችልም።

## እኔ ነኝ ፌዲራሊስት (ኣብሮነት ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ኣንድነት)

ይህ የእነ ልደቱ ኣያሌው (**ኣዲፓ**)፡ ኢንጂነር ይልቃል ጌትነት (**ኢህን**)፡ እና ግርማ በቀለ (**ህብር ኢትዮጵያ**) የተባሉ ድርጅቶች የፈጠሩት ጥምረት ነው። ራሱን **ኣብሮነት ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ኣንድነት** የሚል መጠርያ ስም ይዘዋል። ይህ ስብስብ መሪዎቹ እንደሚሉት ከሆነ ኣሁን ያሉ የህብረ ብሄራዊ ፌዴራሊስቶች ኮንፌዴራሊስት እንጂ ኡነተኛ ፌዴራሊስት ኣይደሉም ይላል። ብክልል ኣምሳል የፈጠሩዋቸው ከፌዴራል መንግስት በላይ የተጠናከረ ሃይል ያላቸው ነፃ ኣገሮች እንጂ በፌዴራል ማእቀፍ የሚገዙ ፌዴራሊስት ኣይደሉም ይላሉ። የክልሎችን ኣወቀቃቀርና በራስ የማስተዳደር መብት ከሞላ ጎደል ይቀበላል። ህገ መንግስቱ ግዲታ ተቀይሮ ለክልሎች የተሰጠውን ሰልጣን ተቀንሶ ፌዲራል መንግስት የበላይ መሆን ኣለበት ይላል።

ይህ ጥምረት ኢዜማና ብልፅግና ተወዳድሮ ወጤት ሊያመጡ ይችሉ ይሆናል ተብለው የሚገመቱ ከኣዲስ ኣበባ እና የኣማራ ክልል ከተሞች ውጭ ሊመወዳደር ይሁን ለማሸንፍ የሚችል ይዘታ የለውም። ይህ ሰብስብ ከወዲሁ የፕሮፓጋንዳው ኣቅጣጫ ፀረ ህብረ ብሄራዊ ፌዴራል ሃይሎች ወደ መሆን ማንጋደዱ ኣይቀርም።

### ማጠቃለያ

ሁኔታዎች በዚህ ፍጥነት ክቀጠሉ በኢትዮጵያ ፓለቲካ የሚከተሉት ክስተቶች ሊታዩ እንደሚችሉ መተንበይና በዚሁ ዙርያ ሀዝብ መማርም ማወቅም ያለበት ቁምነገር ከወዲሁ የሚከተሉት ናቸው።

1. የፈደራሊስቶች መጠቃልልና ወሳኝ ምእራፍ ላይ መድረስ
2. የኣናሳ የፖለቲካ ቡድኖች መክሰም
3. የኣሃዳውያን ብጥብጥ እና ነውጥ በተለያዩ ኣከባቢዎች በተለይ በኦሮምያ ክልል በእምነት ተቋማት፡ እና ዩኒበርስቲዎች፡ እንዲሁም ግድያና መፈናቀል ጭምር ሊበረታታ ይችላል ።
4. በታሪክ እንደታየው የኣንድነት ነን የሚሉ ሃይሎች ስልጣን ካልተቆጣጠሩ ቶሎ እንደሚከስሙ ነው፡ እናም ከምርጫ በኃላ ይከስማሉ ወይ የርስ በርስ ጦርነት ይጠበቃል ብሎ መገመት ይቻላል።